وزارة الصحة
Ministry of Health

Ethiopia

Public Awareness Campaign to Combat Coronavirus (COVID-19)

# በኮረና ቫይረስ (COVID-19) በከፍተኛ ሁኔታ ከተከሰተባቸው አገራት የተመለሳችሁ በባሕሬን የምትኖሩ ዜጎችና ነዋሪዎች በሙሉ፣ የሚከተሉትን ራስን ለይቶ የማቆያ ህጎች ለ14 ቀናት ልትተገብሩ ይገባል።

የተለየ ክፍልና የተለየ የመታጠቢያ ክፍል በመጠቀም ራሳችሁን በመለየት ከሌሎች ሰዎች ጋር የሚኖራችሁን ንክኪ ያስወግዱ፣

ሳህኖችን፣ ኩባያዎችን፣ የመመገቢያ ዕቃዎችን፣ ፎጣዎችን ጨምሮ የቤት ዕቃዎችን ወይም የመኝታ አልጋዎችን ከሌሎች ጋር መጋራትን ያስወግዱ፣

ከሰዎችና ከእንስሳት ጋር በምትሆኑበት ጊዜ የፊት ጭምብል (ማስክ) ይልበሱ፣

በሚያስላችሁና በሚያስነጥሳችሁ ጊዜ አፍና አፍንጫችሁን በሶፍት ሸፍኑ፣ ከዚያም የተጠቀማችሁበትን ሶፍ በቆሻሻ ማጠራቀሚያ መጣሉን ያረጋግጡ፣ እጃችሁን በሳሙናና በውሃ ታጠቡ፣ ወይም ከማስነጠሳችሁ በኋላ ወዲያውኑ በአልኮል ማጽጃ (ሴንሲታይዘር) ያጽዱ፣

እጃችሁን በየጊዜው በሳሙናና በውሃ ወይም በአልኮል ማጽጃ(ሴንሲታይዘር) ይታጠቡ፣

ትኩሳት፣ ሳል ወይም የመተንፈስ ችግር ከተሰማችሁ ወደ (444) በመደወል የህክምና እርዳታ ይጠይቁ፣

**የህብረተሰብ ጤናን በሚመለከት በወጣው ህግ ቁጥር (34) 2018 መሰረትና ከዚህ ጋር በሚዛመዱ ውሳኔዎች መሰረት በተላላፊ ቫይረስ የተያዘን ሰው የደበቀ ወይም ሌሎችን ለቫይረስ ያጋለጠ፣ ወይም ሆን ብሎ ቫረስ ወደ ሌሎች ያስተላለፈ፣ ወይም የቫይስ መዛመትን ለመከላከል የሚወጡ የመከላከያ መንገዶችን ያልተገበረ ማንኛውም ሰው ከ3 ወር ያላነሰ የእስር ቅጣትና ከ1000 የባህሬን ዲናር ያላነሰና ከ10,000 የባህሬን ዲናር ያልበለጠ መቀጮ ወይም ከእነዚህ በአንዱ ሊቀጣ ይችላል።**